በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
ETHIOPIAN BIODIVERSITY INSTITUTE (EBI)

ቀን የካቲት 09 2015
ቁጥር ብዝሀ/185/1123/2015

- ለአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለደቂቅ አካላት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለእንስሳት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለጀኔቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ዳይሬክቶሬት
- ለስርዓተ ምህዳር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
- ለምርምር፣ ስርዓትና ፕሮጀክት ትግበራ ዳይሬክቶሬት
- ለቅርንጫፍ ማዕከላትና ባለድርሻ አካላት ዳይሬክቶሬት
- ለእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት
- ለስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙሰና ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት
- ለንብርትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት

ኢ/ሕ/ኢ

ጉዳዩ፡- **የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎችና ተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት መመሪያ ስለመላክ**

ከላይ የተገለጠውን ጉዳይ አስመልክቶ በጥቅምት 2013 ዓ.ም ለመመሪያ ማሻሻያ የተደረገ ቢሆንም በተከታታይ በትምህርት ሚኒስቴር ከዚያም በግብርና ሴክሬተሪያት ም/ቤት አማካይነት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የግብርናም ሆነ ሌሎች የምርምር ተቋማት መጠቀም የሚችሉት መመሪያ መዘጋጀቱ ይታወቃል::

መመሪያው በዋናነት ለተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገትና ቅጥር አገልግሎት የሚውሉ የህትመት አይነቶች ሳይንሳዊ ይዘታቸው ጥራትን የጠበቀ እንዲሆኑና በምርምር ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች በጉጉት ምርምራቸውን በተሻለ እንዲፈጽሙ አበረታች ሁኔታዎችንም የያዘ በመሆኑ በእኛም ኢንስቲትዩቱ ተቀባይነት አገኝቶ በኢንስቲትዩቱ ተጨባጭ ሁኔታ መመሪያው ተሻሽሎ በተለያዩ ደረጃዎች ከታየ በኃላ በማኔጅሜንት እንዲፀድቅ ሆኗል::

በመሆኑም መመሪያው ከየካቲት 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ለአፈጻጸሙ የራሳቸውን ድርሻ በትጋት እንዲወጡ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ዶ/ር ማርዮ ሰላም(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለዋ/ዳሬክተር /ቤት
- ለም/ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለዋ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት ሃላፊ
- ለውስጥ ኦ/ዲተር ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ኢ/ሕ/ኢ

ስልክ 011-6-612244 ፋክስ 011-6-613722
Tel 011-6-512023 Fax 011-6-612542
011-6-615607 E-mail:info@ebi.gov.et
011-6-616643
ፖ.ሳ.ቁ. 30726
P.O.Box
Web site:www:ebi.gov.et
መልሱን በሚጽፉልን ጊዜ እቦከዎ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱልን
Please quote our Ref. No. when replying
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎችና ተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት መመሪያ

የካቲት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማውጫ

1 የማሻሻያው አስፈላጊነት 3

2 አጭር ርዕስ 4

2.1 ዓላማ 4

2.2 ትርጉም 4

3 የምርምር ህትመት አይነቶች 5

3.1 በኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት ተቀባይነት ያላቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ ሣይንሳዊ የምርምር ሕትመት ዓይነቶች 5

3.1.1 በጆርናል ላይ የሚታተም ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in Journal) 5

3.1.2 በጆርናል ላይ የሚታተም አጭር ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Short communication in Journal) 6

3.1.3 በፕሮሲዲንግ ላይ የሚታተም ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in proceeding) .. 6

3.1.4 የዜና መጽሔት ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in newsletter) 7

3.1.5 የምርምር /የዳሰሳ ጥናት /ሪፖርት (Research /assessment report /working paper) 7

3.1.6 የቴክኒክ ማኑዋል (Technical Manual) 7

3.1.7 በብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም ማዕቀፍ/ መመሪያ (Biodiversity conservation and sustainable utilization guideline) 8

3.1.8 መጽሐፍ (Book) 8

3.1.9 የመጽሐፍ ምዕራፍ (Chapter in a book) 8

3.2 ድጋሚ የሚታተሙ የምርምር ጽሁፎችን በተመለከተ 8

3.3 የተመራማሪዎች የደረጃ እድገት አሰጣጥ 9

3.3.1 የተመሪማሪዎች ደረጃ ዕድገት እና ተፈላጊ መስፈርቶች 11

3.3.2 የተፋጠነ የደረጃ ዕድገት (Accelerated Promotion) 14

3.3.3 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ 14

3.3.4 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 15

4 የመመሪያው ተፈጻሚነት 15

5 መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ 15

6 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች 16

7 የተሻረ መመሪያ 16

መግቢያ

የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ምርምር፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ሥራ በባህሪው ረጅም ጊዜን የሚወስድ፣ በቡድን የሚተገበር እና በቅብብሎሽ ለውጤት የሚበቃ እንደመሆኑ መጠን በሥርዓቱ ተደራጅቶ የሚገኘውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እያበረታቱ ለረጅም ጊዜ በማቆየት ሙያዊ ግዴታውን በተገቢው መንገድ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ተግባርም ከሚጠይቃቸው የተለያዩ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል በግልጽ መስፈርት ላይ ተመስርቶ ወቅቱን በጠበቀና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ ተመራማሪዎች ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚሸጋገሩበት ሥርዓት መዘርጋት አንዱ ነው። በዚህ አግባብ ከጥቅምት 2013 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎች፣ ተመራማሪዎችና የቴክኒክና ላቦራቶሪ ረዳቶች የደረጃ ዕድገት መመሪያን በመከተል የደረጃ እድገት ሲሰጥ ቆየቷል። መመሪያው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ሲተገበር የታዩ ክፍተቶችን በመገምገም ለማስተካከልና ከአገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ ጋር ወጥ አሰራርን በመዘርጋት ተመራማሪዎች በሥራቸው ላይ ተረጋግተው እንዲቆዩ ለማስቻል ነባሩን የእድገት መመሪያ ማሻሻል አንደሚያስፈልግ በሁሉም ዘንድ ታምኖበታል። ስለዚህ በነባሩ መመሪያ ውስጥ የነበሩ የህትመት አያያዝ፣ የቴክኖሎጂ ትርጉምና አያያዝ፣ የስራ ልምድ አያያዝ፣ የቅጥር መስፈርቶች እና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ማሻሻያ ተደርጎባቸው ቀርበዋል።

1 የማሻሻያው አስፈላጊነት

ይህ መመሪያ

- በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎችና ተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት መመሪያ የታዩበትን ክፍተቶች ማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ፤
- በዚህም አግባብ የተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት መሠላል መስፈርትና መለኪያ ግልጽና ተጨባጭ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤
- በኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች አማካኝነት ለህትመት የሚበቁ የምርምር ጽሁፎች ጥራታቸው የተጠበቀ፣ ወቅታዊና ሌሎች ሳይንሳዊ መስፈርቶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ለማስቻል፤
- በምርምር ሥራ ላይ የተሰማሩ ተመራማሪዎች ዕውቀታቸውን እና ጊዜያቸውን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተጠቅመው ጥራት ያላቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ የምርምር ውጤቶችን እንዲያፈልቁ በማስቻል/በማትጋት ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ልማት፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና ለኅብረተሰብ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ዕውቅና ለመስጠት፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Biodiversity Institute
ማርዮ ለላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

- ተመራማሪዎች በዘርፉ የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ በአግባቡ እንዲወጡ፤ በሂደቱም በተመራማሪዎች የደረጃ ስኬል መሰረት ተጠቃሚ ለማበረታታት፤

በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 291/2005 አንቀጽ ቁጥር 8(ለ) እና አዋጅ ቁጥር 120/1990 አንቀጽ ቁጥር 9(3) (ለ) መሠረት ይህ ማሻሻያ መመሪያ ወጥቷል።

2 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎችና ተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት (ማሻሻያ) መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2.1 ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ ተመራማሪዎች የምርምር ውጤቶችን ጥራት ባለው ሁኔታ ተቀባይነት ባላቸውና ታዋቂ (reputable) በሆኑ ጆርናሎች/አሳታሚዎች እንዲያሳትሙ በማድረግ የምርምር ውጤቶች አስተማማኝነትን ማሳደግ፣ ተዓማኒነትን ማረጋገጥ እና የምርምር ጽሁፍ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚያበረክተው ጠቀሜታ ከፍ እንዲል ማድረግ ነው።

2.2 ትርጉም

ለአፈጻጸም ያመች ዘንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹ የተወሰኑ ቃላትና ሀረጎች የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል።

- **"ኢንስቲትዩት"** ማለት የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ነው።
- **"የተመራማሪዎች ፓነል"** ማለት የአመልካች ተመራማሪው ለምርምር እና ለልማት ያሳየውን አርአያነት ለመገምገም የከፍተኛ/መሪ ተመራማሪዎች አባላት ያሉት የዉይይት ቡድን ሆኖ በኢንስቲትዩቱ የሚቋቋም ነዉ።
- **"በፅሁፍ የተመሰከረለት"** ማለት ከታወቀ ህጋዊ የመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ድርጅት ወይም ማህበር አመልካች ተመራማሪው ላስገኘው የምርምር ፋይዳ የሚቀርብ የጽሁፍ ማስረጃ ማለት ነው።
- **"ቴክኖሎጂ"** ማለት የብዝሀ ሕይወት ሀብትና ተያያዥ ነባር እውቀቶችን በሚመለከት ለተጠቃሚዎች የሚደርስ የሥርዓተ ምህዳር/የዝርያ/የንዑስ ዝርያ አጠባበቅ ዘዴ፣ የብዝሀ

ማርዮ ለላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ሕይወት ጥበቃ ሞዴል፣ በባዮፕሮስፔክቲንግ የተገኙና ለቀጣይ ምርምርና ልማት ግብዓት የሆኑ የተለዩ ባህሪያት፣ ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀምና ለጥቅም ተጋሪነት ጥቅም ላይ የዋለ የማሕበረሰብ እውቀት እና ከነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግኝቶችን ያጠቃልላል።

3 የምርምር ህትመት አይነቶች

ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፤ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች / መረጃ ማቅረብን መሠረት አድርገው ከሚሰሩ የምርምር ሥራዎች የተገኙ ውጤቶችን ለተጠቃሚው ለማድረስ ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ህትመት አንዱ ነው። ህትመት የምርምር ውጤቶችን ተደራሽ ከማድረግ ባሻገርም ለተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት፣ ምደባና ቅጥር በመስፈርትነት እያገለገለ ይገኛል። ስለሆነም የተመራማሪዎችን ሣይንሳዊ ጽሑፍ የማዘጋጀት ብቃት ለማጎልበትና የኢንስቲትዩቱን የሕትመት ውጤት ጥራትና ደረጃን ለማስጠበቅ እንዲረዳ ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

3.1 በኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት ተቀባይነት ያላቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ ሣይንሳዊ የምርምር ሕትመት ዓይነቶች

የተመራማሪዎችን ሳይንሳዊ ጽሁፍ የማዘጋጀት ብቃት ለማጎልበትና የህትመት ይዘት ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲረዳ ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚገቡ ህትመቶችን መወሰን አስፈልጓል። ማንኛውም የምርምር ጽሁፍ ለደረጃ ዕድገት፣ ምደባና ቅጥር ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በታወቀ አሳታሚ ድርጅት ወይም ጆርናል ላይ የታተመ ሲሆን ነው። በዚህም አግባብ ደረጃቸውን በጠበቁ አለም አቀፍ ጆርናሎችና በአገራዊ የምርምር እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለቤትነት የሚታተሙ የምርምር ውጤቶች ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ለሳይንሳዊ ህትመቶች ተቀባይነት የሚያስፈልጉ መስፈርት እንደየህትመቱ አይነት ተዘርዝረው እንደሚከተለው ቀርበዋል ።

3.1.1 በጆርናል ላይ የሚታተም ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in Journal)

የጆርናል ጽሁፍ በአንድ በታወቀ የሳይንስ አሳታሚ ተቋም ወይም ድርጅት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ወይም የሙያ ማህበር ወቅቱን እና ሳይንሳዊ ይዘቱን ጠብቆ የሚታተምና ዓለም አቀፍ የመጽሔት መለያ ቁጥር (ISSN) በሚይዝ ሳይንሳዊ ጆርናል ውስጥ የታተመ

ሀ. የምርምር ግኝት ጽሁፍ (Original research article) ወይም

ለ. አገራዊ ጠቀሜታ ባለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥራቱን ጠብቆ የተዘጋጀ ግምገማዊ ጽሁፍ (review article) ነው። ይህን ግምገማዊ ጽሁፍ ወቅታዊና ቀጣይ ጠቀሜታ ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሚዘጋጅ ሆኖ ማዘጋጀት የሚችለው ተባባሪ ተመራማሪ እና ከዚያ በላይ ያለዉ የስራ መደብ ላይ የሚገኝ ወይም ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ተመራማሪዎች ብቻ ነው።

ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ ያለበቂ ግምገማ የሚታተሙ ጆርናሎች ማለትም አጋባሽ ጆርናሎች (predatory journals) ቁጥር እጅግ ተበራክቷል። ስለሆነም ይህን ችግር ለማስወገድ ተቀባይነት ያላቸውን ጆርናሎች መለየት የግድ የሚል ሲሆን መደበኛውን አሠራር በመከተል አዳኝ /በአጋባሽ ጆርናሎች /አሳታሚዎች ዝርዝር (Beal's list of predatory journals/publishers) ውስጥ ያልተካተቱ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ፤ ይህም ሆኖ ሲገኝ የጆርናሉ አሳታሚ ከስድስቱ ታዋቂ ኢንዴክሰሮች (Web of Science, Scopus, PubMed, DOAJ, Scimago, and Sherpa Romeo,) በአንዱ የተጠቀሰ መሆኑን ማረጋጥ ይገባል። ይሁን እንጂ በአገር ውስጥ ባሉ ቀጣይነት ባላቸውና የትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና የሰጣቸው ወይም ከሶስተኛ ዕትም (volume 3) በላይ የሆኑ ጆርናሎች ላይ የሚታተሙ የምርምር ህትመቶች ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በሃገር ውስጥ የታተሙና የትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና ያልሠጣቸው ህትመቶች ላይ ታትመው የጥራት ችግር አለባቸው ተብሎ ከተጠረጠረ ለውጭ ገምጋሚ ተልኮ ጥራቱ እንዲገመገም ሊደረግ ይችላል።

3.1.2 በጆርናል ላይ የሚታተም አጭር ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Short communication in Journal)

በጆርናል ላይ የሚታተም አጭር ሳይንሳዊ ጽሁፍ ከላይ በተ.ቁ. 3.1.1 በተገለጸው መስፈርት መሰረት ተቀባይነት ባለው ሳይንሳዊ ጆርናል ውስጥ የታተመ ሊሆን ይገባል። የዚህ ዓይነቱ ሳይንሳዊ ጽሁፍ በጆርናሎች የመጨረሻ ገጾች አካባቢ Short communication በሚል አምድ ሥር የሚታተሙ እና ይዘታቸው ከዋናዎቹ የጆርናል ጽሑፎች በተወሰነ ደረጃ ያነሰ ነው።

3.1.3 በፕሮሲዲንግ ላይ የሚታተም ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in proceeding)

በፕሮሲዲንግ የሚታተም ሳይንሳዊ ጽሁፍ ማለት በምርምና ልማት ሥርዓቱ አካላት ወይም በሙያ ማኅበራት አዘጋጅነት በሚካሄዱ ኮንፍረንሶች፣ ዓውደ ጥናቶች እና ሲምፖዚየሞች በተመራማሪዎች የቀረቡ የምርምር ጽሁፎችን አጠቃልሎ የሚይዝ ሳይንሳዊ የህትመት ዓይነት ነው። ይህ የህትመት አይነት ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ደረጃ ቁጥር (ISBN) የሚይዝ ሲሆን የምርምርና ልማት ተቋማት ወይም የሙያ ማኅበራት (professional associations) የሚያሳትሙት ይሆናል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Biodiversity Institute
ሰላም(ፒኤችዲ)
ዳይሬክተር

3.1.4 የዜና መጽሔት ሳይንሳዊ ጽሁፍ (Scientific Article in newsletter)

የምርምር እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በአጠቃላይ በአገሪቱ በሚያካሂዱቸው የምርምር እና የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በማተኮር መረጃ የሚቀርብበት፣ በተለያዩ ቋሚ ዓምዶች የተደራጀ፣ በምርምር ማዕከላት የሚካሄዱ ዓበይት ምርምሮችንና ፋይዳቸውን ብሎም የየተቋማቱን እንቅስቃሴ የሚያስቃኝ ዜና የሚቀርብበት እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚደርሱበት የህትመት አይነት ነው። በዜና መጽሔቱ ላይ ታትመው ለግምገማ የሚቀርቡ ጽሁፎች በምርምር ሂደት አልፈው ተቀባይነት ያገኙ የምርምር ውጤቶችና ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ለብዝሃ ሕይወት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀምና ለአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ተጨማሪ ክህሎትና ዕውቀት አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ መረጃዎች መሆን አለባቸው።

3.1.5 የምርምር /የዳሰሳ ጥናት /ሪፖርት (Research /assessment report /working paper)

የምርምር ወይም የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች በአንድ ፕሮጀክት ወይም የምርምር ዘርፍ የተጠናቀቁ ጥናቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እና ተጠቃለው የሚቀርቡበት የህትመት ውጤት ሆኖ የሙያው መስክ የሚጠይቀውን ዕውቀትና ልምድ ባካበቱ ተመራማሪዎች ተገምግሞ በምርምር ተቋሙ ሲፈቀድ የሚታተም እና ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ደረጃ ቁጥር (ISBN) የያዘ የምርምር ህትመት ነው። ይሁንና በአገር ውስጥ ባሉ ዕውቅና በተሰጣቸው የሙያ ማኅበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና በምርምር ተቋማት ዕውቅና የሚታተሙ የምርምር ወይም የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ዓለም አቀፍ የመጽሀፍ ደረጃ ቁጥር (ISBN) ባይኖራቸውም ተቀባይነት አላቸው።

3.1.6 የቴክኒክ ማኑዋል (Technical Manual)

የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ምርምር፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ አረክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች በተለይም የመስክ፣ የላቦራቶሪ እና ወርክሾፕ የአሠራር ሂደቶችንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የሚጠቁም፣ የአተገባበር መረጃ የሚሰጥ፣ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ቅደም ተከተሎች ያሉት ለማጣቀሻነት ወይ ለሥልጠና የሚሆን የህትመት ውጤት ሲሆን በአገር ውስጥ ባሉ ዕውቅና በተሰጣቸው የሙያ ማህበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና በምርምር ተቋማት ዕውቅና የሚታተም ህትመት ነው። የቴክኒክ ማኑዋል ችግር ፈቺ (problem solving) የራሳቸው ዲዛይን ያላቸውና የመጀመሪያ (original) መሆን ይጠበቅበታል።

3.1.7 በብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም ማዕቀፍ/ መመሪያ (Biodiversity conservation and sustainable utilization guideline)

የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ምርምር፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችን በተለያዩ ደረጃ እና ስልት እንዴት መጠቀምና ውጤታማ መሆን እንደሚቻል የሚያስረዳ ዝርዝር መግለጫ ያለው እና ተጠቃሚው በቀላሉ ሊረዳው የሚችል በተቋማት ሲፈቀድ ብቻ የሚታተም ነው። የዚህ ዓይነቱ መመሪያ በቂ የአርትዖት ሥራ ተደርጎበት በተለያዩ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚታተም ነው።

3.1.8 መጽሐፍ (Book)

መጽሐፍ ማለት በአንድ ወይም ተቀራራቢነት ባላቸው የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ምርምር፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በጠለቀ ዕውቀት በተለያዩ ማጣቀሻዎች በመመርኮዝ በወጥነት ወይም በምዕራፍ በተከፋፈለ ሁኔታ የሚዘጋጅ የህትመት አይነት ነው። ይህ የህትመት አይነት ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ደረጃ ቁጥርን (ISBN) የያዘና ታዋቂና ተቀባይነት ባላቸው አሳታሚዎች የታተመ መሆን አለበት። ከድህረ ምረቃ ማጠናቀቂያ ጽሁፍ (MSc thesis and PhD dissertation) በቀጥታ ወደ መጽሐፍ የተቀየረ ሕትመት በዚህ ትርጉም ተቀባይነት የለውም።

3.1.9 የመጽሐፍ ምዕራፍ (Chapter in a book)

ከላይ ለመጽሃፍ የተሰጠው መግለጫ እንደተጠበቀ ሆኖ አርትዖት ተደርጎበት የሚታተም አንድ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ምዕራፍ ሆኖ የሚካተት በአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ጽሑፍ ሲሆን ዋናው መጽሐፍ ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ደረጃ ቁጥር (ISBN) የያዘ መሆን አለበት። ይሁንና በአገር ውስጥ የሚታተሙ የመጽሐፍ ምዕራፍ ዓለም አቀፍ የመጽሀፍ ደረጃ ቁጥር (ISBN) ባይኖራቸውም ተቀባይነት አላቸው።

3.2 ድጋሚ የሚታተሙ የምርምር ጽሁፎችን በተመለከተ

በፕሮሲዲንግስ የታተመ የህትመት ውጤትን ለሁለተኛ ጊዜ በጆርናል ማሳተም ካስፈለገ በፕሮሲዲንግስ ሲታተም የነበረውን የፀሀፊዎች የአስተዋጽኦ ደረጃ ጠብቆ ሊታተም ይችላል። የጆርናል ህትመትን ለማበረታታት እንዲያግዝ በጆርናልና በፕሮሲዲንግስ መካከል ያለው የጆርናል አቻ ዋጋ ልዩነት ለደረጃ እድገት ጠቀሜታ ይኖረዋል። ሆኖም ግን አንድን የምርምር ጽሁፍ በተመሳሳይ ይዘት በተለያዩ ጆርናሎች ወይም በተለያዩ ፕሮሲዲንግስ ማሳተም አግባብነት የለውም።

ማርዮ ለላሞ(ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

3.3 የተመራማሪዎች የደረጃ እድገት አሰጣጥ

ተመራማሪዎች ከነበሩበት ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመሸጋገር በቅድሚያ ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች ውስጥ በምርምር ተቋማቱ ያላቸው የአገልግሎት ዘመን እና በዚሁ ጊዜ ውስጥ ያበረከቷቸው የምርምር ውጤት የሆኑት ቴክኖሎጂዎችና ሳይንሳዊ ህትመቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚሁ አሳቤ ሳይንሳዊ ህትመቶች ተብለው የሚጠቀሱት ከላይ በምርምር ጽሁፍ ህትመት መመሪያ ስር የተዘረዘሩትን የሚመለከት ሲሆን ቴክኖሎጂ/አሰራርን በተመለከተ ደግሞ የብዝሀ ሕይወት ሀብትና ተያያዥ ነባር እውቀቶችን በሚመለከት ለተጠቃሚዎች የሚደርስ የሥርዓተ ምህዳር/የዝርያ/የንዑስ ዝርያ አጠባበቅ ዘዴ፣ የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ሞዴል፣ በባዮፕሮስፔክቲንግ የተገኙና ለቀጣይ ምርምር ግብዓት የሆኑ የተለዩ ባህሪያት፣ ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ጥቅም ላይ የዋለ የማሕበረሰብ እውቀት እና ከነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግኝቶችን ያጠቃልላል።

ሠንጠረዥ1. በተቋሙ ለተመሪማሪዎች ዕድገት የሚያበቁ ተቀባይነት ያላቸው ሳይንሳዊ ህትመቶች ዓይነትና የጆርናል አቻ ግምት ነጥብ ዝርዝር

ተ.ቁ	የህትመት ዓይነቶች	የጆርናል አቻ ግምት
1	የጆርናል ጽሑፍ	1.00
2	መጽሐፍ	3.00
3	የመጽሐፍ ምዕራፍ	0.75
4	የምርምር ሪፖርት	0.50
5	ቴክኒካል ማኑዋል	0.50
6	የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማኑዋል	0.50
7	የፕሮሲዲንግ ጽሑፍ	0.50
8	አጭር የጆርናል ጽሑፍ	0.50
9	የምርምር ዜና መጽሔት	0.10
10	የመፅሀፍ ኤዲተር	0.75
11	የፕሮሲዲንግስ ኤዲተር	0.50
12	አዲስ ቴክኖሎጂ/አሰራር ማመንጨት	1.00

ሠንጠረዥ 2. በሁሉም የጽሑፍ ዓይነት ለፀሐፊዎች (Authors) የሚደርስ የሕትመት ዋጋ ክፍፍል ዝርዝር (በመቶኛ)

የጽሑፍ ዓይነት	አንድ ፀሐፊ	ሁለት ፀሐፊዎች		ሶስት ፀሐፊዎች			አራት ፀሐፊዎች				ከአምስት ፀሐፊዎች በላይ				
	1ኛ	1ኛ	2ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ እና በላይ*
ለሁሉም የጽሁፍ አይነቶችና የቴክኖሎጂ አቅርቦቶች	100	60	40	50	30	20	46	26	18	10	42	25	15	10	9

በኢንስቲትዩቱ በሚታተመው የኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ጆርናል (Ethiopian Journal of Biodiversity) የሚያሳትሙ ተመራማሪዎችን ለማበረታታት፣ የጆርናሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እና በሚመለከተው አገራዊ ተቋም እውቅና (accreditation) እንዲያገኝ ለማስቻል እያንዳንዱ ፀሃፊ በሚያገኘው ነጥብ ላይ የነጥቡ 25% ጭማሪ ይደረጋል። ዝርዝሩም እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 3 ቀርቧል

ሠንጠረዥ 3. በኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ጆርናል (Ethiopian Journal of Biodiversity) ለፀሐፊዎች (Authors) የሚደርስ የሕትመት ዋጋ ክፍፍል ዝርዝር (በመቶኛ)

የጽሑፍ ዓይነት	አንድ ፀሐፊ	ሁለት ፀሐፊዎች		ሶስት ፀሐፊዎች			አራት ፀሐፊዎች				ከአምስት ፀሐፊዎች በላይ				
	1ኛ	1ኛ	2ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ እና በላይ*
በኢ.ብሕኢ. ጆርናል ለሚታተሙ ጽሁፎች X= a+(a*0.25)	125	75	50	62.5	37.5	25	57.5	32.5	22.5	12.5	52.5	31.25	18.75	12.5	11.25

3.3.1 የተመሪማሪዎች ደረጃ ዕድገት እና ተፈላጊ መስፈርቶች

የተመራማሪዎች የደረጃ ዕድገት መሰላልና እና ተፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ተብራርተዋል።

ሠንጠረዥ 4. የተመራማሪዎች ደረጃ ዕድገት እና ተፈላጊ መስፈርቶች

የሥራ መደቡ መጠሪያ	የትምህርት ደረጃ	ተፈላጊ መስፈርት
ጀማሪ ተመራማሪ	ባችለር ዲግሪ	• የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ እና የመመረቂያ ነጥብ ቢያንስ ለወንድ (3.25)፣ ለሴት (3.00) የሆነ፤ የጽሁፍና የቃል ፈተና ያለፈ/ች
ረዳት ተመራማሪ I	ባችለር ዲግሪ	• ጀማሪ ተመራማሪ ሆነው ለ 2 ዓመት የሰሩ እና የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት በአማካይ ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፤ • ወይም ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፤ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) የሁለት ዓመት ሥራ ልምድ ያለው/ያላት፤
	ባችለር ዲግሪ/ ዲቪኤም/ ኢንጅነሪንግ ዲግሪ	• በዲቪኤም ወይም በኢንጅነሪንግ ዲግሪ 0 ዓመት የሥራ ልምድ (በተቋሙ የሚቀጠሩ በተለያዩ የሙያ መስክ በመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ የ5 ዓመት የትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ) የመመረቂያ ነጥብ ቢያንስ ለወንድ (3.25)፣ ለሴት (3.00) የሆነ፤የጽሁፍና የቃል ፈተና ያለፈ/ች
ረዳት ተመራማሪ II	ዲቪኤም/ ኢንጅነሪንግ ባችለር ዲግሪ/ባችለር ዲግሪ	• ረዳት ተመራማሪ I ሆኖ/ና ለ 2 ዓመት የሰራ/ች እና የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፤ • ወይም ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፤ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) የአራት ዓመት ሥራ ልምድ ያለው/ያላት
	ማስተርስ ዲግሪ/ ኤምቪኤስሲ	ተመራማሪዎች የትምህርት ለውጥ በማድረግ ወደ ሥራቸው ሲመለሱ፤- • በማስተርስ ዲግሪ/ ኤምቪኤስሲ በዜሮ ዓመት የሥራ ልምድ በረዳት ተመራማሪ II ላይ ይመደባሉ፣ • ወይም ከምርምር ሥርዓቱ ውጭ የነበረ/ች አዲስ በተመራማሪነት የሚቀጠር/የምትቀጠር፤ ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፤ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) ከሰሩት ውጭ

		በዜሮ ዓመት የሥራ ልምድ ሲሆን የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ነጥብ ለሴቶች 3.00 እና ለወንዶች 3.25 እና ከዚያ በላይ እና የመመረቂያ ጽሑፍ (thesis) ውጤት በጣም ጥሩ (Very Good) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤
ተባባሪ ተመራማሪ	ኤምቪኤስሲ፤ ኢንጂነሪንግ ማስተርስ ዲግሪ	• በረዳት ተመራማሪ II ላይ ለሁለት ዓመት ያገለገለ/ች፣የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፤ ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ0.50 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያለው/ያላት፣ (በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) መሆን አለበት • ወይም ከምርምር ሥርዓቱ ውጭ የነበረ/ች አዲስ በተመራማሪነት የሚቀጠር/የምትቀጠር፤ ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፤ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) በማስተርስ ዲግሪ የ2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት፤ እና ከስራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ 0.75 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያለው /ያላት፤በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሊሆን ይገባል) ።
	ፒ.ኤች.ዲ	• በፒ.ኤች. ዲ ዲግሪ የተመረቁና ዜሮ አመት የስራ ልምድ፤ አግባብነት ያለው የመመረቂያ ጥናት ጽሑፍ ያላቸው እና የ1.00 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያላቸው (በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ)
ተመራማሪ I	ኤምቪኤስሲ/ ማስተርስ/ ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ	• በምርምር ሥርዓቱ ውስጥ ተባባሪ ተመራማሪ ሆነው ለሦስት ዓመት የሰሩ፣ የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ እና የ1.00 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ፣ (በዚህ ደረጃ ከህትመቶቹ ቢያንስ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል እና ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ (first author) ሊሆን ይገባል) ፣ • ወይም ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) በማስተርስ ዲግሪ የአምስት ዓመት ሥራ ልምድ ያለው/ያላት እና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ1.50 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው (የምርምር ጽሁፍ፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) ያለው/ያላት (በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሊሆን ይገበል) ። በዚህ ደረጃ ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ (first author) ሊሆን ይገባል)፣ • ወይም በፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ የሶስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላትና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ1.75 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው (የምርምር ጽሁፍ፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ

		የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) ያለው/ያላት (በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሊሆን ይገባል)። በዚህ ደረጃ ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ (first author) ሊሆን ይገባል)፣
ተመራማሪ II	ኤምቪኤስሲ/ማስተርስ/ ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ	• በምርምር ሥርዓቱ ውስጥ ተመራማሪ I ሆነው ለሁለት ዓመት የሰሩ፣ የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ እና የ1.25 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ፣ (በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል እና ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ሊሆን ይገባል) • ወይም ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) በማስተርስ ዲግሪ የሰባት ዓመት ሥራ ልምድ ያለው/ያላት እና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ2.75 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው (የምርምር ጽሁፍ፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) ያለው/ያላት (በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሆኖ ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ሊሆን/ትሆን ይገባል • ወይም በፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላትና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ3.00 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያለው/ያላት፣ (በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሆኖ ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ሊሆን/ልትሆን ይገባል)
ከፍተኛ ተመራማሪ	ኤምቪኤስሲ/ ማስተርስ/ ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ	• በምርምር ሥርዓቱ ውስጥ ተመራማሪ II ሆነው ለሦስት ዓመት የሰሩ፣ የመጨረሻ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት ከፍተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፣ የ1.50 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ፣ ከህትመቶቹ ቢያንስ ሁለት የግድ ጆርናል አርቲክል እና ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ ሊሆን ይገባል፤ • ወይም ከብዝሀ ሕይወት ማንበር (Conservation)፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር ቀጥተኛና ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች በምርምር ተቋማትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) በማስተርስ ዲግሪ የአሥር ዓመት ሥራ ልምድ ያለው/ያላት እና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ4.25 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያለው/ያላት፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) (በዚህ ደረጃ ቢያንስ ከህትመቶቹ አንዱ የግድ ጆርናል አርቲክል ሆኖ ቢያንስ በአንዱ የጆርናል ህትመት ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ሊሆን/ልትሆን ይገባል፤

		• ወይም በፒ.ኤች. ዲ ዲግሪ የስምንት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላትና ከሥራ መደቡ ጋር ተዛማጅ የሆነ የ4.50 ጆርናል ህትመት ዋጋ ያለው የምርምር ጽሁፍ ያለው/ያላት፣ (በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የጽሁፍ አይነቶችን መሰረት ያደረገ) በዚህ ደረጃ ህትመቶቹ ሁሉ የግድ ጆርናል አርቲክል ሆነው ቢያንስ በአንዱ የጆርናል አርቲክል ላይ የመጀመሪያ ፀኃፊ /first author/ሊሆን/ልትሆን ይገባል)።

3.3.2 የተፋጠነ የደረጃ ዕድገት (Accelerated Promotion)

ተመራማሪዎች ከተለመደው አሰራር በተለየና ከሚጠበቅባቸው በላይ ጉልህ ውጤት ማስመዝገብ ሲችሉ የፊጠነ የደረጃ ዕድገት የሚታይበት አግባብ መኖሩ ተመራማሪውን ለበለጠ ሥራ የሚያተጋና የተወዳዳሪነት መንፈስን የሚያጠናክር እንደሚሆን ይታመናል። ስለዚህም የፊጠነ የደረጃ ዕድገት ዕድል እስከ ከፍተኛ ተመራማሪ ድረስ ለሚኖረው ደረጃ ብቻ የሚሰጥ ሆኖ በሁለት መንገድ ማየት ያስፈልጋል።

ሀ) ድርብ እርከን ዕድገት (Double Promotion)

ለዚህ የደረጃ ዕድገት የሚያበቃ መስፈርት የሚጠይቀው አንድ ተመራማሪ ለቀጣይ ደረጃ የሚያበቃውን መስፈርት ከማሟላት በሻገር አገራዊ ፋይዳ ያለው ውጤት ያስመዘገበበት የምርምር ስራ ሲኖረው ወይም በይፋ የሚታወቅና ፈታኝ ሆኖ የቆየን ቁልፍ የብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀምን፣ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት እና የስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ችግር መፍታቱን በተለየ የሙያ መስክ የተመሰከረለት የምርምር ውጤት ሲያገኝ አንድ ደረጃ እንዲዘል ይደረጋል።

ለ) ከጊዜ ገደብ ቀድሞ የሚሰጥ የደረጃ ዕድገት (Early Promotion)

ተመራማሪዎች ካሉበት ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለማደግ የሚያስፈልገው ጊዜ ሳይደርስ ለማደግ ለደረጃ ዕድገቱ የሚጠይቀውን የስራ ልምድ ማሻሻና ከዚያ በላይ ካገለገሉ እና ለደረጃ ዕድገቱ የተቀመጠውን ሳይንሳዊ ጽሑፍ (የጆርናል) ህትመትን በእጥፍ ከሚሉ የደረጃ እድገት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ አሰጣጥ ተጠቃሚ የሚሆኑት ከተባባሪ ተመራማሪ ጀምሮ ያሉት የሆናል።

3.3.3 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የታተሙ የምርምር ሕትመቶች ጥቅምት 2013 ዓ.ም ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎች፣ ተመራማሪዎችና የቴክኒክና ላቦራቶሪ ረዳቶች የደረጃ ዕድገት መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ። ይህ መመሪያ ከወጣ በኋላ ለአንድ ዓመት ያክል ጊዜ ለደረጃ እድገት የሚያመለክቱ ተመራማሪዎች ለዕድገቱ የሚያቀርቧቸው ጽሁፎች በዚህ መመሪያ ላይ ባልተካተቱ ኢንዴክሰሮች የታተሙ ሆነው ሲገኙ

የሚዳኙበትም ሆነ የሚጠየቅባቸው ነጥብም ጥቅምት 2013 ዓ.ም ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ባለው መስፈርት ሲሆን፣ ይህ መመሪያ ከፀደቀ በኋላ የሚታተሙ ጽሁፎች ግን የግድ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን እስካላሟሉ ድረስ ተቀባይነት አይኖራቸውም ።

3.3.4 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

- የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱ ተመራማሪዎች ባስገኙት የትምህርት ደረጃ ለውጥ መሰረት ሀትመት ሳይጠይቅ ከረዳት ተመራማሪ I እስከ ተመራማሪ II ባሉ እርከኖች አንድ የደረጃ ዕድገት ይሰጣቸዋል፤
- ተመራማሪዎች ለዕድገት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ሳያሟሉ ቀርተው በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለደረጃ ዕድገት ባይበቁና ዘግይተው ዕድገቱን ቢያገኙ የአገልግሎት ዘመናቸው ለዚሁ ዕድገት እንጂ በትርፍነት ተይዞ ለሚቀጥለው የደረጃ ዕድገት አያገለግልም፤
- በኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት በዋናው መ/ቤት በዋና ዳይሬክተርነት፣ በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት በዘርፍ ዳይሬክተርነት እና በማዕከላት ዳይሬክተርነት የተሰየሙ ኃላፊዎች ቢያንስ 3 አመት ካገለገሉና ለደረጃው የሚያስፈልገውን የሀትመት ዋጋ 50% ካስመዘገቡ የኃላፊነት አፈጻጸም የሥራ ድርሻቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቃቸውን በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች ሲረጋገጥ የመሪ ተመሪማሪነት ደረጃ ዕድገት ሲቀር በሌሎቹ እርከኖች የአንድ ደረጃ እድገት ይሰጣቸዋል። ሆኖም ግን አንድ የሥራ ኃላፊ በተቋሙ ውስጥ በሚኖረው ቆይታ በኃላፊነት ዕድገት የሚሰጠው ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም ከብቃት ማነስ ጋር ሳይገናኝ በኢንስቲትዩቱ አሰራር ምክንያት ሁለት አመትና ከዛ በላይ አገልግለው ከቦታው የሚነሱ ሃላፊዎችም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።
- በተመራማሪነት በአዲስ መልክ የሚቀጠሩ ተመራማሪዎች ከምርምር እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓቱ የተገኘ የስራ ልምድ ካላቸው በቀጥታ የሚወሰድ ሲሆን ከብዝሀ ሕይወት ማንበርና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ጋር ተዛማጅ የሆኑ ተግባራትን በሚፈጽሙ ሌሎች ተቋማት በተሰጠ አግልግሎት የተገኘ የስራ ልምድ በግማሽ (50%) የሚያገ ይሆናል፤

4 የመመሪያው ተፈጻሚነት

- ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

5 መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

- ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ የሚሻሻል ይሆናል።

6 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

- ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም በኢንስቲትዩቱ የወጣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም

7 የተሻረ መመሪያ

- ከጥቅምት 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለውን የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የሥራ መሪዎች፣ ተመራማሪዎችና የቴክኒክና ላቦራቶሪ ረዳቶች የደረጃ ዕድገት መመሪያ ተሽሯል።

9/6/2015

መለሰ ማርዮ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

የካቲት 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ